የረቡዕ ጥር 26 1997 ዓም( የጃንዋሪ 26 2005)

# የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## <u>ለወያኔ ሽፋን ለመስጠት ሲባል በምርጫ መሳተፍ÷ ዴሞክራሲን አያስገኝም</u>

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ÷ በአምባገነናዊነቱ በመቀጠል÷ ተቀዋሚ ኃይሎች ለነፃ ምርጫ መካሄድ ዋስትና ብለው ያቀረቧቸውን ቅድመ ሁኔታዎች አልቀበልም ብሏል፡፡ የራሱን የተጭብረበረ ምርጫ÷ መሠረት ሊሆንለት የሚችል ህግን ፓርላማ በሚለው ስብስቡ አፀድቋል፡፡ ተቃዋሚ ኃይሎች በሰላም በፖለቲከው ሂደት ተሳታፊ ሆነው በሕዝብ ውሳኔ ተገዝተው ለመታገል አይፈልጉም እያለ ሲቀጥፍ የነበረውን አገዛዝ በማሳፈር÷ ድርጅቶቹ ተባብረውና በይፋም በነፃ ምርጫ ለመሳተፍ ዝግጁ መሆናቸውን ገልጠው እንደነበረም የሚታወስ ነው፡፡ የመለስ ቡድንም÷ ሳይወድ በግዱ በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፉ ሁኔታዎች ተፅዕኖ ÷ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር መደራደርን ተገደደ ፡፡ ሆኖም÷ ድርድሩ ጊዜ መግዣና ገንዘብ ለጋሾች ባዕዳንን ማወናበጃ እንጂ ከልብ በመነጨ ቀና መንፈስ ያልተጀመረ መሆኑ ያኔም ሆነ አሁን ግልፅ ነው፡፡

ተቃዋሚ ኃይሎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ለነፃ ምርጫ አስፈላጊና ወሳኝ የተባሉትን ዘርዘረው አቅርበው ወያኔ እነዚህን ከተቀበለ እነሱም በምርጫ ለማሳትፍ የሚያግዳቸው ምንም ነገር እንደማይኖር አስታውቀው ነበር፡፡ የመለስ አገዛዝ ለራሱ የበላይነት ማረጋጋጫ አመቻችቶ ያወጣው ዴሞክራሲን መብትን የሚፀረር የምርጫ ህግ እንዲያሻሽል÷ እንዲለውጥ ጠየቁ፡፡ በወያኔ ቁጥጥር ስር ያለው የምርጫ ቦርድም÷ ተነስቶ ነፃና ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ እንዲመሰረት ጠየቁ፡፡ የዓለም ኣቀፍ ታዛቢዎችም እንዲገኙ ጠየቁ፡፡ ወያኔ ከዚህ ሁሉ አንገራግሮ የተቀበለው የባዕድ ታዛቢዎችን መገኘት ሲሆን÷ ከዚህ ቀደም በተካሄደው ምርጫ የተገኙ ባዕዳን÷ ወያኔ አጭበርብሯል ወዘተ ቢሉም÷ ያመጡት ለውጥ ስላልነበረ÷ ይገኙ ብሎ መቀበሉ እምብዛም ለውጥ አለመሆኑ ለማንም አልተሰወረም፡፡ ለራሱ ክልል በምርጫው ህግ ያደረገው አድልዖና ይበልጥ ወኪል የመስጠት እርምጃ እርምት ሊያደርግ ቀርቶ÷ አይነሳብኝ ከማለቱ ሌላ ከተቀዋሚው ኢዴኃን ጋር ሲወያይም ታዛቢ መኖሩን

አልቀበልም ብሎ ነበር። በመሀልም ዋና ጉዳይ ያልሆነውን ዋና አድርጎ በማቅረብ፥ ማለትም እነ ኢሕአፓ ዓይነት ድርጅቶች ዋስትና ወረቀት ይፈልሙልኝ ብሎ በመጠየቅ ውይይቱን ፈር ሊያስለቅቅም ሞክሮ ነበር። ህገ ወጥ የተባሉ ድርጅቶች መሪዎች ይፋ ቢወጡ፥ ጉዳት እንደማይደርስባቸው ዋስትና ለመስጠት ዝግጁ ያልሆነው ወያኔ፥ ከዚህ ቀደም እነ አቶ አበራ የማነአብን ከማሰሩ በፊት እንደለፈፈው ማንም ቢመጣ አይታሰርም ብሎ ከመመፃደቅ ባሽገር፥ ቁም ነገር ያለው አቅዋም ሊያሰማ አልቻለም። ብትመጡ አትታሳሩምን ሰምተው ዛሬም ከአስራ አንድ ዓመት በኋላ በቃሊቲ የሚሰቃዩትን እን አቶ አበራ የማነ አብን እንኳን ከእስር ሳይፈታ፥ ያመለጣችሁኝ ኑና ታሰሩልኝ ማለቱን መርጧል። መለስ፥ የተቃዋሚ ድርጅቶችን፥ ሳሩን አይቶ ወደገደል እንደተወረወረ በሬ መቁጠሩ፥ ከራሱ በስተቅር ማንንም ሊያታልል አይችልም።

ተቃዋሚ ኃይሎች የተባሉት፥ በምርጫ ለመሳተፍ በቅድሚያ የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱልን ብለው በጎብረታቸው ደረጃ ከቶም አልጠየቁም። ይህ ቢያሳዝ ም፥ ወያኔ ቅድመ ሁኔታ ተደረደረብኝ ብሎ ሊያላዝ የሚችልበት ዕድል አልነበረውም ማለት እንችላላን። ተቃዋሚ ኃይሎች ይሻሻልና ፥ ይለወጥ ያሉት፥ ነፃ ምርጫን ህልም የሚያደርገውን የምርጫ ህግ ነው። ይለወጥ ያሉት በወያኔ ሹሞች የተሞላውንና ለመለስ ታዛዥ የሆነውን የምርጫ ቦርድ ነው። የመለስ ቡድን እምቢ አሻፈረኝ አልቀበልም፥ አለወጥም ያለውም ይህንኑ ነው። ስለዚህም የመጪው ግንቦት ምርጫ ውጤት፥ ሳይታለም የተፈታ፤ ሳይደረስ የታወቀ ነው። ከዚህ በፊት ከአንዴም ሁለቴም አይተነዋልና እንግዳ ነገር አይሆንብንም ። ወያኔ ይሸነፍ ይሆናል፤ 40 በመቶ ወንበር ይለቅልን ይሆናል፤ ዛሬ ተንገዳግዶ ከአምስት ዓመት በኋላ ይወድቅልናል ወዘተ እያሉ ሳይጨፈሉ የሚሞኙ፥ ወይንም ሕዝብን ለማሞኘት የሚሞክሩትን ክፍሎች ማዳመጥ ደግሞ፥ ጅልነትና ሀገረና መብትን ማስጠቃት ይሆናል። የመለስ ቡድን ሊሸነፍ የሚችለው፥ ነፃ ምርጫ ሲደረግ ብቻ ነው። የምርጫውን ህግ ለራሱ አመቻችቶ፤ የምርጫውን ቦርድ ተቆጣጥሮ፤ፖሊሱ፤ ካድሬው፥ ጦሩና ቢሮክራሲው የራሱ ሆኖ ባለበት፥ የሚሮጠው ከራሱ ነውና ማሸነፉ የሚያጠራጥር አይደለም። መለስ ዜናዊ ከተለመደው መሸበሩ ቀነስ ካደረገ በቧልቱ ለሚያጅቡት፥ ከበፊቱ ትንሽ በለጥ ባለ ደረጃ ወንበር ሊፈቅድላቸው ይችል ይሆናል። ቀጭን ተስፋ ናት ነገሪቷ። ባለፈው መርጫ ባዕዳን ከተቃዋሚ መቶ ያህሉ ወንበር ቢያገኝ አገዛዝህ ሳይለወጥ መልኩ ያምራል ብለው ቢመክሩት፥ አሻፈረኝ ማለቱን እናስታውሳለን። ወያኔ ከተሸነፈ፥ ሽንፈቱን ይቀበላል እስከማለት መቃዡት የጀመሩ ክፍሎች፥ በኢትዮጵያ ነዋሪ ነን ቢሉ መጠራጠራችን ሲያንስ ነው። መለስ ዘነዊ

ደግሞ በተለመደው ጮሌነት ይህንኑ አጉልና ጫጩት ተስፋ፥ በመጫኛ ለመጣል 60 በመቶ እናሸንፋለን ሲል ተደምጧል:: አሞኘን በሞቴ የሚሉት ክፍሎች ደግሞ፥ 40 በመቶ ልናገኝ ነው ብለው ከወዲሁ መፈንደቅ ጀምረዋል:: ክስተቱ አሳዛኝ፤አሳፋሪና ክህደት ነው ቢባል አግባብ አለው::

የመለስ ቡድን፥ አርሶ አደሩን በመሬትና በማዳበሪያ ክፍያ እያስፈረራ፤ በገፍም እያሰረ ፤ ባለፈው ምርጫ በደቡብ እንዳየነውም እየረሸነ በቁጥጥሩ ስር ማዋሉ የማይቀር ነው:: ሌላው ክፍልም፥ በየፈርጁ ምሱ ተዘጋጅቶለታል:: ሳጥን ቅየራውም ይካሄዳል:: በሁለትና በሶስት ቦታዎችም የሚመርጡ መኖራቸው አይቀሬ ነው:: የመለስ ዜናዊ ሚስት ወልቃይት ሳይሆን፥ የአዲስ አበባ አራዳ ተመራጭ ሆና ብዙሀኑ በፍቅር ድምፅ ይሰጧታል:: ይህ የማያስቅ ቧልትና ቲያትር ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ፥ ስሙ፥ ተቀበሉ፥ የምንባለው ነው:: ወያኔ ኢሕአዴግ አሸናፊ ይሆናል:: መለስ ዜናዊም ሕዝብ መረጠኝ ብሎ በጠቅላይ ሚኒስቴርነት ሀገር በማጥፋት ተልዕኮው ይቀጥላል:: ይህ ነው የሚጠብቀን ዕውነታ፤ የነገ ክሰተታችን:: ሌላ አልነበረም፤የለም፤ አይኖርምም:: ወያኔን በዚህ ፀረ ዴሞክራሲ ሂደቱ ሊያጅቡት ወስነው የሚገኙት ደግሞ እንደተመኙት እንኳን 40 በመቶ አሸናፊ ቢባሉ ፥ የሚመጣው መሰረታዊ ለውጥ የለም:: የስልጣን ማጠየቂያ ጦሩንና የአፈና ኃይሉን የሚቆጣጠረው የመለስ አገዛዝ ነው:: ፓርላማ ተብዬው ራሱ ፋይዳ እንኳን በቅ ብሎበታል ቢባል፥ ወያኔ በአብዛኘው እየተቆጣጠረው ባለበት ወንበር መያዙ ሽፋን ለመስጠት እንጂ፥ ለሕዝብ ፋይዳ ለማምጣት አለመሆኑ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ፤ያየነው ያወቅነው ጉዳይ ነው:: ፓርላማ ሲባል፤ሸንጎ ሲባል ከዚህ ቀደምም አይተናል:: ለአባላቱ ደሞዝ አስገኝቶ ካልሆነ በቀር ለሕዝብ የፈየደው አልነበረም፤ ዛሬም እንደሌላ 13 ዓመታት አሳይተውናል:: የራሴ ያለውን ፓርላማ እንኳን ሳያማክር፥ አምባገነኑ ባፈተተው እየወሰነና የሀገርንም ሕልውና ሳይወረር እየቸረቸረ ነው::

የተቃዋሚ ኃይሎች ግብ፤የሀቀኛ ሀገር ወዳድ ድርጅቶች ዓላማ፥ መለስ ዜናዊን ማጀብ ወይም ሽፋን መስጠት ሳይሆን፥ ከእነ አገዛዙ ማንኮታኮት፤ማስወገድ ነው:: ሥልጣን በወያኔ እጅ ተይዛ፥ በወያኔ ፓርላማ ባለወንበር መሆን ዓላማዬ ነው የሚል ድርጅት መቸም ተቃዋሚ ነኝ ሲል፥ ሳቅ ቢይዘን፥ ሊፈረድብን አይገባም:: ነፃ ምርጫ ሊካሄድ የሚችለው ደግሞ፥ አሁን መለስ ዜናዊ ባፀደቀው ህግ መሠረትና በሚቆጣጣረው የምርጫ ቦርድ አማካኝነት አይደለም:: ለዚህም ነው ሀቀኛ ድርጅቶች የምርጫው ህግ እንዲለወጥና ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ እንዲሰየምም የታገሉትና እየተጋሉም ያሉት:: ዛሬም

ቢሆን፥ ይህ ትግል አልተቋረጠም፡፡ መቀጠልም ያለበት ነው፡፡ ህጉ ባይለወጥም፤ቦርዱ ነፃ ባይሆንም፥ በምርጫው እንሳተፋለን ማለት ሳይሆን፥ ተቃዋሚ ኃይሎች አብረው ሕዝብን በማነሳሳት፥ የነፃ ምርጫ ህግ እንዲከበር መታገልና ማታገል አለባቸው፡፡ በጦርነት ከመተናነቅ፥ በውጊያ ከመተላለቅ፥ በሰላም መወዳደሩ ይበጃል ብለው በኅብረቱ የተሰበሰቡት ድርጅቶች ሁሉ፥በነፃና በርቱዓዊ ምርጫ ለመወዳደር ተዘጋጅተው ታይተዋል፡፡ ህገ ወጥ የተባሉትና በኢዴኃኅ የተሰባሰቡት ድርጅቶችም፥ የዚሁ አካል ነበሩ/ናቸው፡፡ የነፃ መርጫውን በር ገርበብ ማድረግ ሳይሆን፥ ክርችም አድርጎ የዘጋው እነሆ ወያኔ ነው፡፡ ይህንን ለሕዝብም ለባዕዳንም በሚገባ ግልፅ አድርጎ መሳየት ያሻል፡፡ የመለስ አገዛዝ ነፃ ምርጫ ማለት፥ ለእርሱ ሽንፈት ማለት መሆኑን ያውቃልና በሕዝብ ትግል ሳይገደድ ሽንፈቱን አይቀበልም፡፡ ቀና ህሊና የሚባልም ስለሌለው፥ በድርድር ብቻ የሚቀበልና የሚገባው  አይደለም፡፡ ለዚህ ነው ሕዝብን ለቆረጠ ትግል ማነሳሳትና ማሰለፍ የሚገባው፡፡ ነፃ መርጫ መብታችን ነው ብሎ ሕዝብ መታገል አለበት፡፡ ይህንን ትግል የሚያደናቅፉ ደግሞ ሰልፋቸው ከወያኔ እንጂ፥ ከሕዝብ አልመሆኑን ከወዲሁ መረዳትና ማወቅ እንዳለባቸው በጊዜ መንገር ያሻቸዋል፡፡

ወያኔን በፀረ ሕዝብ ቧልቱና ፀረ ዴሞክራሲ ምርጫው ማጀብ ሳይሆን፥ ለሕዝብ፥ ለህቀኛና ነፃ ምርጫ፥ ለሀገርና  ለሕዝብ ለሚበጅ ለወጥ መታገል ማለት፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዘላቂ ጥቅም፥ ለሀገራችን ዘላቂ ሠላመና አስተማማኝ መረጋጋት ተገኘ ማለት ደግሞ፥ ልማትና ዕድገት ዋስትና አገኘ ማለት ይሆናል፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ፥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት መሠረት ይጣላል ማለት ይሆናል፡፡  ያለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ደግሞ ሠላምና አስተማማኝ መረጋጋት ሊመጣ አይችልም፡፡ ወያኔ በሥልጣን ላይ እያለ፥ ይህ ክስተት የሚታለም አይሆንም፡፡  መለስ ዜናዊንና ዘረኛ  ሥርዓቱን ማስወገድ ኃላፊነትና ተልዕኮ ደግሞ የከሌ የከሌ ሳይባል የሁሉም ኢትዮጵያዊ ነው፡፡  ታጋይ ተሰማራ ትግሉን ልትመራ የሚለው ጩከት  ነው ጩኸታችን፡፡ ታጋይ አደብ ግዛ ፓርላማ እንድትገባ አይደለም የእኛ መርሆአችን፡፡ ኢትዮጵያን ለማዳን ያለው ምርጫ ወያኔን አስወግዶ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መተካት ብቻ ነው፡፡

በትግላችን መብታችንን እናስከበር!!!